# ግፍ የትም ይሁን የትም ያው ግፍ ነው፡፡

(ሰብዓዊ መብትን ከሚጥሱ ጋር ማበር ጸረ ሰብዓዊ ያደርጋል)

ከናትናኤል

ነጻነታችን ተጣሰ፣ ዲሞክራሲያዊ መብታችን ተገፈፈ፣ ፍትህ አጣን ብለን አምርረን በመታገላችን ታሰርን ተገረፍን፣ ተረሸን ግን ቀዳዳ ስናገኝ ደግሞ ተሰደን ሕይወታችን አቆየን፡፡ በዓለም ዙሪያ የተሰደድን ባገር ላለው ሕዝባችን መብት መከበር ብለን በጸሃይና በበረዶ በብርሃንና በጨለማ ጩኸታችንን እነዚህ ሃያላን አገሮች ይሰማሉ በማለት ድምጻችን ኢትዮጵያ አስኪሰማ አስተጋባን፡፡ መቼም ከነዚህ ሃያላን አገሮች ተሰሚነትን መጠበቅ እንድ "የበሬ ምናምን ይወድቅልኛል ብላ እንደምትጠብቅ ቀበሮ" አድርጎናል፡፡

በኢትዮጵያ በየጊዜው የሚነሱብንን አምባገነን ገዥዎችን በመፋለሙ ያገር ልጆች ከፍተኛ ታሪካዊ ስራዎችን አከናውናል፡፡ የዚያውን ያህል አሳፋሪ ልጆቿ በወያኔና መሰል ድርጅቶች ውስጥ ተሰግስገው አገራችንን ለማፍረስ ጥረታቸውን ከመቼውም ጊዜ በላይ አፋፍመው ይገኛሉ፡፡ ሃቀኛ ኢትዮጵያውያን ወያኔን የምናወግዘው በጠባብነቱ ነው፣ በአምባገነንነቱ ነው፡፡ በፀረ ኢትዮጵያዊነቱ ነው፡፡ጸረ ዲሞክራሲ በመሆኑ ነው፡፡ በፀረ ፍትህ ተግባሩ ሕይወታቸውን ለማቆየት ከወያኔ የሚሸሹት ስንት ኢትዮጵያውያን በረሃው ውጦ አስቀርቶቿል፣ ስንቶቹ የአውሬ ሲሳይ ሆነዋል፣ ስንቶቹ በበሽታ ረግፈዋል፣ ስንቶቹስ ናቸው ባሕር የዋጣቸው፡፡

ሃቀኛ የኢትዮጵያ ልጆች ከወያኔ መወለድ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የሞት ሽረት ትግል ላይ ናቸው፡፡ ዛሬ ባገር ቤትና በውጭ አገር የሚታየው የሕዝብ ቁጣና እንቅስቃሴ ወያኔ ምንኛ ጊዜ የጨለመበትና የተደናበረ ጌኛ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያመላክታል፡፡ ወያኔን ከስልጣን ለማውረድ የጎደለን አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ አስመሳዩንና ሃቀኛውን ታጋዮች በሚገባ ለይቶ ከጎናቸው በመቆም ሕዝባዊ አመራራቸውን መደገፍ ነው፡፡ ግልጽ ከሆነ ጠላት ጋር መፋለሙ የሚከብድ አይሆንም፡፡ አንዳንድ ድርጅቶች ያዋጣኛል ብለው የሚከተሉት ያጭርና የረጅም ዘዴያቸው ጠላትን ከማዳከም ይልቅ ሲያጠናክሩ ብዙ ጊዜ አስተውለናል፡፡

ብዙ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" የሚለውን አካሄድ ባላጤኑት ጎዳና ሲወስዱት ይታያሉ፡፡ ከለላ ምሽግ ያስፈልገናል፡፡ ጥቃት የደረሰባቸውን ታጋዮቻችንን የምናስታምምበት ቦታ ያስፈልገናል፡፡ የመሳሪያና የገንዘብ እርዳታ ያስፈልገናል በማለት ካገር ውጭ ጦራቸውን እንዳስቀመጡ ይነገራል፡፡ የአገሩን መሬት ለውጭ ጦር የሚለቅ አገር ያለጥቅም እንዲህ አይነቱን ደግነት ያደርጋል ብሎ ማመን የዋሕነት ነው፡፡

ዛሬ ከምድረ ኤርትራ የሚታየው የሕዝብ ግፍ ኢትዮጵያ ካለው ግፍ የሚያንስ ወይም ያልተለየ ነው፡፡ ልክ እንደ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች የኤርትራ ስደተኞችም በረሃው ፈጅቶአቸዋል፣ የአውሬ ሲሳይ ሆነዋል፣ ገሚሱም በባሕር ሰምጠው ሕይወታቸው ተቀጭቷል፡፡ ሕይወታቸውን ያጡት እኒህ የኤርትራ ተወላጆች የሚሸሹት ከራሳቸው መንግስት ነው፡፡ ቀብጠው ሳይሆን ግፉ ስለበዛባቸው ነው፡፡ሁለቱ ስደተኞች መንገዳቸው አንድ ነው፡፡ ፍትህ ዲሞክራሲና ነጻነትን ፍለጋ ነው መንገዳቸው፡፡

ሻቢያ ልክ እንደ ኢትዮጵያው ወያኔ ግፈኛ ጨቋኝና ገዳይ ነው፡፡ ልክ እንደ ወያኔ ሻቢያም ፀረ ፍትህና የሰብዓዊ መብትን የሚጥስ በዳይ መንግስት ነው፡፡ ፍትህ ዲሞክራሲንና ነፃነትን ለሚሻው ሁሉ ከሻቢያና ከወያኔ ደጅ ሊያገኛቸው አይታሰብም፡፡ ወያኔንና ሻቢያን የሚደግፍ ግለሰባ ድርጅት ወይም አገር ያው እንደነሱ ግፍን የሚያራምዱ ናቸው፡፡ የወያኔን ጭቆና የሚጠላና የሚታገል ሁሉ በኤርትራ ሕዝብ ላይ ሻቢያ የሚያወርደውን የግፍ አገዛዝ አጥብቆ ሊያወግዝ ይገባዋል እንጅ ደጋፊ መሆን አይጠበቅበትም፡፡

ፋሺስቱን ወያኔ አውግዞ ከፋሽስቱ ሻቢያ ጋር መወዳጀት ቢወርድ የፓለቲካው ሀ ሁ  ያልገባው ሲጦዝ ደግሞ ግልገል ፋሺስት መሆን ነው፡፡

**"ኢትዮጵያ ከወያኔ ነጻ ትውጣ እንጅ ከሰይጣንም በተባበር ካለብኝ እተባበራለሁ"** የሚሉ ማሞ ቂሎ አይነት ግለሰቦችና ድርጅቶች ያስተዋልንበት አሳዛኝ ዘመን መደረሱ በራሱ ኣሳፋሪ ነው፡፡ ለኔ እንደሚረዳኝ ከሆነ ከሰይጣን የሚወዳጅ ሴይጣን እንጅ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡  ኤርትራ ዛሬ የጸረ ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ማፍለቂያ ፋብሪካ ሆናለች፡፡ በጸረ ኢትዮጵያዊነት ራሳቸውን በምድረ ኤርትራ በሻቢያ ቡራኬ የፈጠሩ ጠባብ ብሄርተኛ ድርጅቶችን መቁጠሩ ያታክታል፡፡ በሺ የሚቆጠሩ ታጣቂዎችን አሰልጥነናል የሚሉም የሽምቅ ተዋጊ ነን የሚሉም ብዙ ናቸው፡፡ ለመሆኑ የስንቅና ትጥቁን አቅርቦትእንዴት ይችሉታል? አለን ሲሉን አመታት ተቆጠሩ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ዘልቀው ወያኔን ሲያስደነግጡ ግን አልሰማንም፡፡ ኢሳትም እንዴት አድርጎ ማውራት እንደሚችልም ጥናት እያደረገ ነው፡፡

ግፍ የትም ይሁን የትም ያው ግፍ ነው፡፡ በወያኔ ሲሰራ ግፍ የተባለውን ያህል በሻቢያም ሲደገም ያው ግፍ እንጅ ነጻነት ሊሆን ከቶም አይቻልም፡፡ ገዳዩን ወያኔ ገዳይ ማለቱ ትክክል ነው፡፡ ገዳዮን ሻቢያን ግን የነጻነት አባትና ኤርርትራምዲሞክራሲ የተንሰራፋበት አገር አድርጉ ማውራት ትክክል አለመሆን ብቻ ሳይሆን በሚሰቃየው ኤርትራዊያን ቁስል ላይ አሲድ ማርከፍከ ነው፡፡ ወያኔ ግፍን እንጅ ነጻነትን አያውቅም፡፡ የዚያውኑ ያህልም ሻቢያ ስለሚያካሄደው ባርነት ያውራ እንጅ ስለነጻነት ሊናገር አይችልም፡፡ ሻቢያ በራሱ ሕዝብ የተጠላው ግፈኛና አምባገነን ሃይል ነው፡፡

በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሺነር በሰጠው መረጃ መሰረት ኤርትራ "ነጻ" ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ ለስደት የተዳረጉት የኤርትራ ልጆች ቁጥር ከ305,000 በላይ ደርሷል፡፡ ሻቢያ የታዳጊ ሕጻናትን ሰብዓዊ መብት በመርገጥ ዕድሜያቸው 15 ዓመት የሆኑትን በውትድርና እያሰለጠነ ይገኛል፡፡ በጡረታ መገለልና መረዳት የሚገባቸውን የ50፣60ና 70 ዓመት አዛውንቶችንም መሳሪያ እንዲሸከሙ አድርጉኣል፡፡ ከወታደራዊ አገልግሎት የሚሸሹትን ቤተሰብ በገንዘብ እስከ $3,333 (50,000 ናቅፋ ብር) ይቀጣቸዋል፡፡ ዛሬ ውጭ የሚኖሩ ኤርትራውያን ወደ አገራቸው ለመግባት ኤርትራ ነጻ ከወጣችበት ከ1992 ጀምሮ ከገቢያቸው 2% ታክስ መክፈል አለባቸው፡፡ ይህን ክፍያ በማይከፍሉ ላይ ነጋዴ ከሆኑ የንግድ ፈቃዳቸውን ይቀማል፡፡ ቤት ንብረታቸውን ይወርሳ፡፡ ውጭ ካሉ ቤተሰባቸው እንዳይገናኙ መብት ያሳጣቸዋል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ኤርትራ በሚገርም ሁኔታ ከነጻነት ቀን አንድ እስከዛሬ ድረስ አገሪቷ የምትመራው ያለ ሕገመንግስት ነው፡፡ ሁሉንም ስልጣን የያዘው ኢሳያስ አፈወርቂ ነው፡፡ ያንድ ሰው ፋሺስታዊ አምባገነንነት የነገሰባት ኤርትራ ችግር ውስጥ ናት፡፡ ሻቢያ በኤርትራ ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰቱ ሞልቶ ፈሷል፡፡

ትናንት አንዳንድ ድርጅቶች በሁለገብ ትግሉ የሚያምኑትን ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን በተለይም በጦር መሳሪያ ወያኔን እናወርደዋልን የሚሉትን "ጠመንጃ ነካሽ" እንዳላሉ ሁሉ ዛሬ ያለ መሳሪያ ወያኔ መጣል አይቻልም ከሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሳቸው እሰየው ያሰኛል፡፡ መሳሪያ አንስቶ መታገሉ ግን የግድ በፋሺስቱ ሻቢያ ድጋፍ መሆን አይገባውም፡፡ ምንም ምክንያት ይደርድሩ ምንም ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ ጫካ ተራራ ሸለቆ ያላት አገር ናት፡፡ የሽምቅ ውጊያ ለማድረግ ታመቻለች፡፡ ደኑ ቢጠፋም እንደተራራ ደን ሸለቆ ሊሆን የሚችል ጀግና ሕዝብ አላትና ትግሉ ኤርትራ ድረስ መፈርጠጥ አይገባውም ምናልባት ኤርትራ የተመረጠው ኢትዮጵያ ጀግና ሕዝብ ደን ሸሎቆ የለውም ከሚል ቅዥት ተገብቶ ከሆን፡፡

ከሻቢያ መጠጋት ሻቢያ በሕዝቡ ላይ የሚያወርደውን ሰቆቃ አልሰማሁም ወይም አላየሁ ማለትና ይመስላልና ይህን መሰል ዓይን ያወጣ ስህተት የምትሰሩ ሁሉ ልቦና ይስጣችሁ፡፡ ሌሎቹን ሁሉ ልተውና ግንቦት 7 ከሻቢያ ጉያ ውስጥ መወሸቁ የሻቢያን ብቻ ሳይሆን የግንቦት 7ንም ኢሰባዊነትና ጸረ ሕዝብነትን

ነው የሚያመላክተኝ፡፡ ግንቦት 7 ዕውነተኛ ነጻነት ዲሞክራሲና ፍትህ ያልገባው ወይም ቢገባውም ባህሪው እንዳልሆነ ቁልጭ አድርጎ አሳይቶናል፡፡ ስለ ነጻነት ያልገባቸው ሻቢያም ሆነ ወያኔ ለሕዝባቸው የሰጡት ነጻነትን ሳይሆን ባርነትን ነው፡፡

ለግንቦት 7 አንድ ሃቅ ግልጽ ሊሆንለት ይገባል፡፡ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ ወዳጅ እንጅ ጠላት አይደለም፡፡ በሌላ አነጋገር የኢትዮጵያ ሕዝብ የኢሳያሱ ሻቢያ ወዳጅ አይደለም፡፡ ከድጡ ወደ ማጡ ሆኖ ግንቦት 7 ምናልባት ሊወጣው ከማይችለው መቀመቅ ወርዷል፡፡ ምናልባትም ይህ የተበላሸ የትግል ዘዴው ለወያኔ የ2015 ልይ ስጦታው የሆነለት ይመስለኛል፡፡ ሩጫው ሁሉ ወያኔን ለመጣል ብቻ መሆን የለበትም፣ ወያኔስ ከወደቀ በኋላስ መደረግ ያለበት ምንድ ነው ብሎ ከወዲሁ መዘጋጀት ካገር ወዳዱ ሁሉ ይጠበቃል፡፡ በሻቢያ የሚገኝ ነጻነት ከተመክሮ እንዳየነው ነው የሚሆነው፡፡ ሻቢያ ወያኔን ለሰባት አመት አሽመድምዶ ኢትዮጵያን ገዝቷል፡፡ አሁን ሕልሙ ከተሳካለት ለበለጠ ዓመታት ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ እንዳትሆን ነው የሚፈልገው፡፡ ለነገሩ ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን ከወያኔ በራሱ ትግል ነጻ ያወጣል፡፡ የጊዜ ጉዳይ ነው!